# የመኢአድ ደጋፊዎች እርባና ቢስ ዋይታ

ስሞኑን በየፓልቶኩ እየተዘዋወርኩ የሚደረጉትን ውይይቶች ሳዳምጥ ባብዛኛው ውይይታቸው ያተኮረው መኢአድ ከወያኔ ጋር ያደረገው የስነምግባርና የምርጫ ስምምነት ላይ ሲሆን ፤ በሁለተኛ ደረጃ ተከታትሎ የሚወያዩበት  የቀድሞው አነግ ነጋሶ ጊዳዳና የቀድሞው ወያኔ ስዬ አብረሃ የአንድነትን ፓርቲ መቀላቀል ላይ ያተኮረ ሆኖ አግኝቼዋለሁ ። ለዛሬው በመኢአድ ላይ ላተኩርና በሚቀጥለው በአንድነት ላይ ያለኝን ግንዛቤ አካፍላችኋለሁ ።

መኢአድ ከወያኔ ጋር ያደረገው መፈራረም ትክክል አይደለም የሚለው ወይንም መፈራረሙን የሚቃወመው ኃይል ሚዛን የደፋና መከራከሪያ ነጥባቸውም አግባብነት ያለውና መሰረታዊ ሆኖ ሳለ ፣ በአንፃሩ የመኢአድ ደጋፊዎች ነን የሚሉት ግን መሪያችን የሚሉትን ኢንጅነር ኃይሉን እንደ ጣኦት የሚያመልኩ ፤ መሪያቸው ሊታመን የሚገባው ፤ የማይሳሳት ፤ የሚሰራውን የሚያውቅ ፤ አገሩን ወይንም ኢትዮጵያን አሳልፎ የማይሰጥ እና የመሳሰሉትን ከተጨባጭ ሁኔታ ጋራ ሲተያይ ግን ማረጋገጫና ማስረጃ ማቅረብ ያልቻሉ ተከራካሪዎች እንዲያው በደፈናው እምኑን ኢንጂነሩንም እንመናቸው ብቻ የሚሉ ደካማዎችና መሰረት የሌላቸው ሆነው አግኝቻቸዋለሁ ።

የመኢአድ ደጋፊ ነን ብለው እራሳቸውን የሚጠሩት ግለሰቦች መኢአድ ከዚህ ቀደም መኢአድ ከመሆኑ በፊት የቅንጅት አንዱ አካል እያለና ከዚያም ቅንጅት ተከፋፍሎ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ከተፈጠሩም በኋላ መኢአድ እራሱን ችሎ አንድ የፖለቲካ አካል ሆኖ ከወጣ በኋላ ይዞት የነበረው ባለ ስምንት ነጥብ ቆይቶም ወደ ሰባት ነጥብ ከወረደው የመታገያና የማታገያ ነጥባቸው ዋልታ የሆነውን ፣ በስልጣን ላይ ያለው አገዛዝ ሊያከበርልን ይገባል ብለው ያቀረቡት ጥያቄ አሁን ካደረጉት ድርድር ውስጥ ለምን እንዳልተካተተ ሲጠየቁ ይሄ ነው የሚባል አጥጋቢ መልስ ለማቅረብ አልቻሉም ። በተለይም የምርጫ ቦርዱ ገለልተኛ መሆንን በተመለከተ እንኳን ደጋፊ ነን የሚሉት የድርጅቱም መሪ በዚህ ጉዳይ በአንድ ወቅት ተጠይቀው ስንካላ የሆነና ውሃ የማይቋጥር መልስ ሰጥተው ማለፋቸው ይታወሳል ።

በጣም ካሳዘነኝ አንዱ የመኢአድ ደጋፊዎች መከራከሪያ ነጥባቸው ፤ እዚህ በዲያስፖራ ያለው እኔ አውቃለሁ ወይም ተምሪያለሁ የሚለው ነው እንጂ መኢአድ የወሰደውን እርምጃ የሚቃወመው አገር ቤት ያለው ሕዝብ በጅምላ የደገፈው አድርገው ለማቅረብ መሞከራቸው አስገርሞኛል ። ሁላችንም በስደት የምንግኝ ኢትዮጵያውያኖች በሐገርቤት ወዳጅ ዘመድ ያለንና የፖለቲካውን ሁኔታም ከወዳጅ ዘመዶቻችን የሚነገረን እንደሆነ መዘንጋታቸውና አለማስተዋላቸው ከምን የመጣ ይሆን? <u>ያም እንኳን አጥጋቢ አይደለም ቢባልም ባመታዊው ታላቁ እሩጫ ውድድር ሁልጊዜም ይወገዝ የነበረው  በስልጣን ላይ ያለው ወያኔ እንደነበረ ሁላችንም እናውቃለን ፤ በዘንድሮው እሩጫ ግን ወያኔ መሆኑ ቀርቶ የተወገዙት የመኢአዱ መሪ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ናቸው ።</u> ህዝቡ ላውግዞት የተጠቀመበትን ቃል ጆሮ ለራሱ ባዕድ ይሁንና ፣ የዲያስፖራው የመኢአድ ደጋፊዎች እንዳይከፋቸው ቃሉን ከመጠቀም ተቆጥቤአለሁ ። ይህም የሆነበት ምክንያት ከማንም የተሰወረ አይደለም ፤ ወያኔን አፍቅረው መኢአድን ጠልተው ሳይሆን መኢአድ የወሰደው እርምጃ ስላሳዘናቸው እንጂ ። ታዲያ ያ በታላቁ እሩጫ የተሳተፈው የዲያስፖራው ሰው ነው ሊሉን ይሆን? ወይንስ የኢትዮጵያ ሕዝብ አይደለም ሊሉን? የኢትዮጵያ ሕዝብ ማለት ያ በሩጫው ላይ የተሳተፈው ሕዝብ ካልሆነ ከሌላ ፕላኔት ሌላ ኢትዮጵያዊ ሊያመጡልን ነው? ምን አይነት አፍዝ አደንግዝ ሀቁን ሰወረባቸው ?

አንድ ድርጅት ወይንም የድርጅት መሪ ሲሳሳት ፣ ተሳስተሀል አካሄዱ ሊታረም ይገባል ብሎ ሂስን መሰንዘር ድርጅቱን ወይንም ግለሰቡን ቆም ብሎ እንዲያስብና ሂሱንም መርምሮ የራሱንም አካሄድ አጢኖ መንገዱን ለማረም ይረዳዋል እንጂ ሂሱ የሚጎዳው አይሆንም ፤ ሆኖም ግን በመኢአድ አመራሮችና ደጋፊዎቹ አካባቢ ይህ ሁኔታ እንደ አፍራሽነት አንዳንዴም እንደ ጸረ ዲሞክራሲና ጸረ ኢትዮጵያዊነት አድርገው ሊያቀርቡት ሲሞክሩ ስመለከት በድርጅቱ ውስጥ ሳያውቁት አምባገነናዊ ፈላጭ ቆራጭና ግለሰባዊ ተክለሰውነት ለመትከል እየተሯሯጡ እንደሆነ ለመረዳት አስችሎኛል ።

በመሰረቱ የመኢአድ መሪዎችም ሆኑ ደጋፊዎቻቸው በስልጣን ላይ ካለው ከገዢው ወያኔ ጋር በምን በምን ሁኔታዎች ላይ እንደተስማሙ ቁልጭ ብሎ የተቀመጠ አንድም ነገር ሊያበረክቱልን አልቻሉም ፤ ሁሌም ከመኢአድ አካባቢ እንደሚመጣው የተድበሰበሰና ግልጽ ያልሆነ ወይንም በሰምና ወርቅ መሰል የሚቀርብ እንቆቅልሽ መሰል ለመፍታት የሚቸግር ሆን ብሎ የሚሰነዘር የማደናገሪያ ዲስኩር እንጂ ።

ሰሞኑን አንድ ሁኔታው በጣም ያሳዘነውና ነገሩን ያጤነ ግለሰብ ሲናገር የተፈራረሙት የምርጫ ደንብና ስነምግባር ሳይሆን "ወያኔያዊ ግብረገብነት " ነው የተፈራረሙት በማለት በጥሩ አማርኛ አስቀምጦታል ። እውነትም የወያኔ ግብረገብ የሚያሰኝ ነው ።

በዚሁ የግብረገብነት ፊርማ ላይም አንዱ ድርጅት ሌላውን ድርጅት እንዳይከስ ፣ እንዳያጣጥል ፣ ስህተቱን እንዳይናገር ከሆነ የተፈራረሙት ታዲያ ለሕዝቡ እኔ ከዚህኛው ድርጅት እሻላለሁ ፣ ጥቅምህንና ፍላጎትህን አሟላልሀለሁ ፤ መብትህን አስከብርልሀለሁ ብለው ሊያስተምሩትና ሊቀሰቅሱት የሚችሉት ምን ተናግረው ፣ ምን ይዘው ፣ በምን አሳምነው ነው? በመሰረቱ ወያኔ ይህንን መፈራረሙን የመረጠው ሊያሸንፉ የሚችሉበትን ነጥብ እንዳያነሱ ካነሱ ግን የተፈራረሙበትን ውል እንዳፈረሱ ተቆጥረው ከጨዋታው ውጪ ሊሆኑ እንደሚችሉ ብሎም በእስራትም ይሁን ከዚያም ከፍ ባለ ሁኔታ ሊያስጠይቃቸው እንደሚችል አድርጎ እንደሚሆን ለመገመት አያዳግትም ።

ሕዝብ ወያኔን እንደጠላ ፣ ወያኔን እንደማይመርጥ ወያኔዎች እራሳቸው ከማንም በበለጠ አበጥረው ያውቁታል ። ሆኖም ግን ወያኔ የ2002ን ምርጫ ለማሸነፍ ካድሬዎቹን ለአምስት አመት ያሰለጠነና ሁሉንም በየክፍለ ሐገሩ አስቀድሞ ያሰማራ ፤ ካለፈው ከ97ም ምርጫ በደንብ የተማረ መሆኑንና ያለፈውንም ስህተቱን በዚህኛው ምርጫ ላይ እንደማይደግም ደጋግሞ ነግሮናል ። ሰሞኑንም አንድ ከዲያስፖራው የሄደ አፍቃሪ ወያኔ የሆነ ጋዜጠኛ ነኝ ባይ የወያኔ ቁንጮ መለሰ ዜናዊን በቪዲዮ ቃለመጠይቅ አድርጎለት የወያኔው ቁንጮ ምን ያክል በልበ ሙሉነት ምርጫውን አሸናፊ ሆኖ እንደሚወጣና ያለፈው ስህተት እንደማይደገም አሁንም አይናቸውን ላልገለጡ ተቃዋሚ ነን ባዮች ዳግም አረጋግጦላቸው አልፏል ። አድማጭ ካለ!

ስለሆነም ተቃዋሚ ነን ብለው አሁን ከገዢው ጋር የተፈራረሙት የፖለቲካ ቡድኖች ሕዝብን ሊቀሰቅሱና ሊያስተምሩ ብሎም እነሱን እንዲመርጣቸውና በነሱ ላይ ሕዝብ እምነት እንዲኖረው ለማድረግ ያላቸው በጣም አጭር ጊዜ በመሆኑ ፣ ሚዲያውንም ወያኔ ሰፍሮ የሚሰጣቸው እንጂ እንደ ገዢው ወያኔ ያለገደብ የሚፈነጩበት ስላልሆነ የማሸነፍ እድላቸው እጅግ የመነመነ ብቻም ሳይሆን ጭራሽ የለም ለማለት የሚያስደፍር ይሆናል ።

ተቃዋሚው እራሱ የሚታረድበትን ካራ ስሎ ላራጁ ለወያኔ ስላስረከበ እንጂ በዚህ በአጭር ጊዜም ቢሆን ሕዝቡን ከጎናቸው ማሰለፍና ምርጫውንም በድል አድራጊነት ሊወጡት በቻሉ ነበር ። ያ ግን ሊሆን አልቻለም ከወያኔ ጋር የተፈራረሙት ሊያሸንፉ የሚችሉበትን ነጥብ ለሕዝብ ማንሳትም ሆነ ማሳወቅ  እንደሌለባቸው ስለሆነ እንደማያሸንፉ እያወቁት ወያኔ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት እንዲያገኝ የወያኔ ተባባሪና አጃቢ በሌላ መልኩ የሕዝብ ተፃፃራሪ ሆነው ለመጓዝ ሳይገደዱ ወደው የገቡበት ስለሆነ አላገናዘቡም ለማለት አያስደፍርም ።

በመሰረቱ ተቃዋሚው ለሕዝብ ይፋ አድርጎ ቢናገርና ቢያስተምር ሊያሸንፍባቸው የሚችልባቸው አበይት ነጥቦች ውስጥ ከብዙው ጥቂቱን ለመዘርዘር እወዳለሁ ። እነዚህ ነጥቦች ግን በምርጫው ወቅት ከማንኛውም ተቃዋሚ ነኝ ከሚል የፖለቲካ ድርጅት ለህዝብ ይፋ እንደማይሆኑ ስለተስማሙበት የሞተ ጉዳይ ነው ፤ ሆኖም ግን አንባቢያን እንዲያውቋቸው ነጥቦቹን በቅደም ተከተል እነሆ፡-

፩ ኛ- በምዕራብ ኢትዮጵያ ከሰሜን ጎንደር እስከ ገሙጎፋ ርዝመቱ 1600 ኪ/ሜትር የሆነና ጥልቀቱ ከ30 እስከ 60 ኪ/ሜትር የሚደርሰው ለም መሬታችን ለሱዳኖች መስጠቱን ማንም ተቃዋሚ ነኝ የሚል ድርጅት በምርጫው ወቅት ሕዝብን ለማነሳሻና ለመቀስቀሻ ሊያነሷቸው ወይም ሊጠቀሙባቸው እንደማይችሉ ፤ እነዚህን አንገብጋቢ ጉዳዮች ቢያነሱ በተቃዋሚው ድርጅት ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ጣጣ ተቃዋሚ ነን ባዮቹ እንዲያውቁት ወያኔ አስቀድሞ ይፋ ያደረገላቸው ስለሆነ ይህ ጉዳይ በምንም አይነት መንገድ በምርጫው ላይ ሊነሳ እንደማይችልና ያደባባይ ሚስጥርም ሆኖ እንዲቀር ተስማምተውበታል ።

፪ ኛ- በመሀል አገር ለም መሬቶች እየተመረጡ ገበሬዎች ለዘመናት ከኖሩበት ቀዬ እየተፈናቀሉ እጅግ በጣም ሰፊ የሆኑ መሬቶች ለባእዳን ለ90 አመት በኮንትራት (ሽያጭ) መልክ በሄክታር $0.25 ሂሳብ መቸብቸቡ ፤ ይህ የባዕዳን የርሻ መሬትን መቆጣጠር ለአገር የማይበጅ ደሃውንም አርሶ አደር መሬት አልባ ከማድረጉም ባሻገር ፤ ከቦታው የሚገኘውም ምርት ለሀገር ፍጆታ የሚውል ሳይሆን ለባህር ማዶ ሽያጭ እንጂ ፤ የተራበው ባለመሬቱ በገንዘቡም እንኳን ገዝቶ ለግል ፍጆታ ሊያውለው እንደማይችል ባለፈው የሳውዲ ከበርቴዎች ባገራችን አምርተው ካገኙት የሩዝ ምርት በሙሉ በመርከብ ተጭኖ ወደ ሳውዲ መጓዙን አስመልክቶ ሁኔታው ወዴት እያመራ እንደሆነ ከቅርቡ ጊዜ ትዝታ መማር ይቻላል ፤ ይህ የውጭ ዜጎች  የእርሻ መሬትን መቆጣጠር ሊያመጣ የሚችለውን ጣጣ

ለማወቅ ዚምባዌን መመልከቱ ጥሩ ማስረጃ ይሆናል ። ስለሆነም ይህ ጉዳይ ለህዝብ ይፋ ያደረገ ተቃዋሚ ሁሉ ውጉዝ ከማሪዎስ እንዲሆን ተባብለው ስለተፈራረሙበት ሕዝብን የማደራጃና የማንቀሳቀሻ መሳሪያ ሆኖ ማንም ሊጠቀምበት እንደማይችል አስምረውበታል ።

፫ ኛ- በቅርቡም የተገኘው የወርቅ ፤ የፖታሽና የሌሎችም የማዕድን ድልብ ቦታዎች ወያኔ ምናልባት ነገ ከስልጣን ልንወገድ እችል ይሆናል በማለት ከስግብግብ ፅባዩ በመነሳት ለሀገርና ለወገን ሳይቆረቆር ለሳውዲና ለሌሎች ምዕራባውያን ዜጎች ባወጣ ያውጣ በማለት በግድየለሽነት በርካሽ ዋጋ የሸጠውና ገንዘቡንም ወደግል ካዝና ያዘዋወረ መሆኑን እንዳይተነፍሱም ተማምለዋል ።

፬ ኛ- ህፃናት ልጆች በወያኔ በተደራጁ አፋኝ ቡድኖች ከእናቶቻቸው ጉያ እየታፈኑ እናቶችም የደም እንባ እንዲያነቡ እያደረገ ለዜጎችና ለወገን ግድ የሌለው ፤ ሕዝብን በማስለቀስ ታላቅ እርካታን የሚያገኘው አረመኔው ወያኔ ህፃናትን በመላው ዓለም ለገበያ እንደ ሸቀጥ በማቅረብ ልጆች ከናታቸው ጡት ተነጥለው በማያውቁት ዓለም እንዲኖሩ እየተገደዱ ፤ ከወላጆቻቸው ፤ ከወንድምና እህቶቻቸው ፤ ካደጉበት ቀዬአቸው በጉልበት ታፍነው የወያኔ የውጪ ምንዛሪ ማግኛ ሆነው ያሉበት ሁኔታ መሆኑን ለሕዝብ ይፋ እንዳይደረግ ተስማምተውበታል ።

፭ ኛ- ወጣት ልጃገረዶች እያጭበረበሩና እየደለሉ በየአረብ አገሩ ለባርነትና ለፍትወት ማርኪያ ፤ ለዘላለም ባርነት እየዳረጓቸው መሆኑን ፤ በዚህም አሰቃቂ የንግድ ሁኔታ ተጭበርብረው ለባርነት የተዳረጉት ህፃናት እህቶቻችንና ልጆቻችን በአሰቃቂ ሁኔታ በየእለቱ ህይወታቸው በገዛቸው ባሪያ አሳዳሪው እጅ በአሰቃቂ ሁኔታ እየተገደሉ አሊያም ከሰቆቃው ለማረፍ ሲሉ የራሳቸውን ህይወት በየእለቱ እያጠፉ እንደሆና ይህም ሁኔታ ድብቅነቱ ለኢትዮጵያዊው እንጂ በውጪው ዓለም በሰፊው እየተዘገበበት መሆኑን እንዳይታወቅ ማድረግና የመሳሰሉት ሁሉ ወያኔን ከስልጣን ሊያወርዱ ፤ የህዝብንም አይበገሬ ቁጣ ሊቀሰቅሱ ስለሚችሉ ይህንን ላያነሱበት ቃላቸውን ሰጥተው ወደው የገቡበት የኢትዮጵያን ሕዝብ በፊርማቸው የካዱበት ሰነድ ነው ።

፮ኛ-በተጨማሪም ባገር ቤት ንግድን በተመለከተ ሁሉም ነገር የሚካሄደው በኤፈርት ስር ወይም በኤፈርት መልካም ፈቃድ ነው ። ያም ብቻ ሳይሆን ትላልቅ የንግድ ፈቃዶች የኮንስትራክሽን ጨረታዎች አለተወዳዳሪ ወይንም ለይስሙላ ተወዳዳሪን በማቅረብ አሸናፊው ቀድሞ በተወሰነ የውስጥ ስራ ሁሌም ለኤፈርት እንደሚሰጥና ነጋዴው በሀገሩ ሰርቶና ነግዶ እንዳይበላ ከትላልቅ የንግድ ተቋሞችና እስከ አነስተኛ የኪዮስክ ንግዶች በዚሁ ኤፈርት በሚባለው በወያኔ ለወያኔ በተቋቋመው የዘረፋ ቡድን እየተካሄደ ያለውንና ወገን ሰርቶ እንዳይበላ እንደ ጋሬጣ የሆነውን የገዢውን ዋልታ ማጋለጥና ድርጊቱን ለህዝብ ማሳወቅ እነደማይቻል የስምምነታቸው አንዱ አካል ነው ።

በመጨረሻም በኔ እይታ ከላይ የተዘረዘሩትን 6 ነጥቦችንና ሌሎችንም አያሌ ህብረተሰባችንን አነቃቂና አነሳሽ የሆኑ ጉዳዮች ሕዝብን ሊያስቆጡና ለአመጽም ሊጋብዙ ስለሚችሉ እነዚህን ያገርና የወገን አንገብጋቢ ጥያቄዎችን አለመንካት ወያኔን የሚያስፈራውን ያክል የተቃዋሚውንም ቡድን እንደማይመቹት ለመገንዘብ አላዳገተኝም ። የሕዝብን አመጽ ከወያኔ ባልተናነሰ መልኩ እራሳቸውን በተቃዋሚነት ያሰለፉትም ቡድኖች እንደሚፈሩትና ሕዝብም አልገዛም ብሎ እንዳይነሳ ወያኔ የሚታገለውን ያክል እነዚህ ተቃዋሚ ነን ባዮችም ወያኔ የሕዝቡን አመፅ ለማፈን በሚያደርገው ርብርብ ከፍተኛ እርዳታና አስተዋፅኦ እያደረጉለት ነው ። ይህማ ባይሆን ኑሮ የተደረገውን ድርድር ብዕርን አውጥቶ ለመፈረም ቀርቶ በጨዋታ ውስጥ አስገብቶ ለመወያየት ባልተቀመጡ ነበር ።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎችም አያሌ ወያኔ እየፈጸማቸው ያለውን አስቃቂ ሁኔታዎች ማንሳት በማይቻልበት ሁኔታ ወደምርጫው ገብተን ሕዝቡን እንታደገዋለን ማለት እራስን ከማታለል ሊያልፍ ስለማይችል የተፈራራሚዎቹም ሆነ የደጋፊዎቻቸው ዋይታና ለቅሶ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለመግደል ከሚደረግ ትግል ያለፈ ሊሆን ስለማይችል ይልቅስ አቋምንና አመለካከትን አስተካክሎ ሳይመሽባቸው ወደ ሕዝብ ጎራ ቢቀላቀሉ ይመረጣልና ልቦና ይስጣችሁ እላለሁ ።

አይምሮ ዳኛቸው